# ምድብ ሁለት (ከ1ኛ — 3ኛ) ክፍል

## 39 ኛ ሳምንት

## አማላጅነት

*መግቢያ*

- ልጆቹ ቅዱሳን እንደማይሞቱ መረዳት አለባቸው። ቅዱሳን ይህንን ዓለም ትተው በሰማያዊው ዓለም መኖር ይጀምራሉ። በዚያም እንደመላዕክት ከእኛ ጋር ለመገናኘት ነፃ ናቸው። በተለይ ደግሞ የኛን ደካማ ጸሎት በእነርሱ ጸሎት ያግዙታል።

*ጥቅስ*

- "የፃድቅ ሰው ጸሎት በሥራዋ እጅግ ኃያል ታደርጋለች።" የያዕቅብ መልዕክት 5 ፥ 16

*ንባብ*

- የዮሐንስ ራእይ 3 ፥ 8 ፣ 8 ፥ 3 - 4፣ የዮሐንስ ወንጌል 2 ፥ 1 — 10።።
- የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ታሪክ፡ በብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ ካልዕ።

*መግቢያ*

- በቤተክርስቲያን ስለሚገኙ ስለእመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም፣ መጥምቁ ዮሐንስና፣ የመላእክት ሥዕሎች ለልጆቹ ጥያቄ ያቅርቡላቸው።
- የቅዱሳን ሥዕላት ፊታቸው ወደኛ ሆኖ የሚሰቀለው ለምንድር ነው?
- በቅዱሳን ሥዕሎች ላይ ካህኑ ዕጣን የሚያጥነው ለምንድር ነው?
- በእመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ምልጃ በቃና ዘገሊላ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እንዴት በሠርጉ ላይ ተአምር እንዳደረገ ለልጆቹ ይተርኩላቸው። የዮሐንስ ወንጌል 2 ፥ 1 — 10።

*የትምህርቱ አጭር መግለጫ*

- ስንሞት ሥጋችን በድን ይሆናል። ነፍሳችን ግን ወደ እግዚአብሔር ትሔዳለች። የፃድቃን ነፍስም ወደ ገነት ትሔዳለች በምድር ካሉት ጋርም ግንኙነቷን ትቀጥላለች።
- በሰማያት ያሉት ነፍሶችና እኛ የአንዲት ቤተክርስቲያን ልጆች ነን። እነርሱ በገነት ናቸው እኛም ወደ እነርሱ እስክንሄድ ድረስ በምድር ላይ እንኖራለን። በሰማያት ያሉት ቅዱሳን በፍቅር የተሞሉ ስለሆኑ በጸሎታቸው እኛን ይደግፉናል ያስቡናል። እኛን ይሰሙን ይሆን? አዎን በደንብ ነው የሚሰሙን።
- ልክ ሳናየው ከሩቅ ቦታ በስልክ የምናነጋግረውን ሰው ድምጽ እንደምንሰማው ሁሉ እኛም ስንጸልይ ቅዱሳን የኛንም ጸሎት ይሰማሉ። ጸሎታችሁን እንደ መንፈሳዊ ሞባይል ስልካችሁ ልትቆጥሩት ትችላላችሁ። በመንፈሳዊ ሞባይላችን ጸሎት ተጠቅመን የእመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያምን ፣የምንወዳቸውን መላእክት ወይም ቅዱሳን ስም ስንጠራ ጸሎታችን ኃይል ይኖረዋል።
- ለምሳሌ አባታችሁን አንድ ነገር ብቻችሁን ብትጠይቁት ነው ወይስ ወንድም እህትና እናታችሁ አግዘዋችሁ ብትጠይቁት ነው ቶሎ ምላሽ የምታገኙት? እነርሱ ካገዟችሁ ነው የሚፈጥንላችሁ። ከሰማያዊ አባታችንም ዘንድ ያለው ሁኔታ ተመሳሳይ ነው። መልካም ነገር የምንጠይቅ ከሆነ የቅዱሳን እገዛ አግኝተን የጸለይነው ነገር ይደረግልናል። የቅዱሳኑም ፍቅር ተካፋይ እንሆናለን።
- ቅድስት ማርያም መላእክትና ቅዱሳን በእግኢብሔር ዙፋን ዙሪያ ናቸው። ዘወትር ስለኛ ይጸልያሉ ይማልዳሉ። አማላጅነታቸውን በምንጠይቅበት ጊዜ በኛ ጸሎት ላይ የእነርሱን ጨምረው ለእግዚአብሔር ያቀርባሉ።
- ይኸውም እመቤታችን በቃና ዘገሊላ ሠርግ ላይ እንዳደረገችው ማለት ነው። ለኛ የማይጠቅመን ወይም ሊጎዳን የሚችል ነገር ከጠየቅን ቅዱሳኑና መላእክቱ ጸሎታችንን አስተካክለው ለኛ በሚጠቅመን መልኩ ይማልዱልናል።
- ካህኑ መሠውያውን በዕጣን ሲያጥን እኛ የማናያቸውና እነርሱ ግን የሚያዩን ቅዱሳንና መላእክትን እንዲያማልዱን እንጸልያለን። ልመናችን ለእግዚአብሔር ነው ቅዱሳንና መላእክት ግን ያማልዱናል። ከኛ ጋር አብረው እየጸለዩ ጸሎታችንን ወደ እግዚአብሔር ያደርሳሉ። በቅዱሳንና መላእክት አማላጅነት እግዚአብሔር ጸሎታችንን እንዲቀበል በትህትና ቆመን ወደ ሰማዩ አባታችን ልንፀልይ ይገባል።

*ማጠቃለያና ጥያቄ*

- ካህኑ በቅዱሳንና መላእክት ሥዕል ላይ ዕጣን የሚያጥነው ለምንድር ነው?
- መላእክቱ ይሰሙናል ወይ? ቅዱሳን ሲያርፉ ነፍሳቸው የምትሄደው ወደ የት ነው?
- ቅዱሳን ከዚህ ዓለም ከተለዩ በኋላ እኛን ይሰሙናል ወይ?
- ቅዱሳን ያሉት በሰማይ ከሆነ እኛ ደግሞ እዚህ ምድር ላይ ከሆንን እንዴት ሊሰሙን ይችላሉ?
- ጸሎታችን የሚቀርበው ለቅዱሳኑ ወይስ ለእግዚአብሔር? ከቅዱሳንና ከመላእክት ለእግዚአብሔር የሚቀርበው ማነው?
- ከእኛ እና ከእመቤታችን ከቅድስት ድንግል ማርያም ጸሎት የማን ጸሎት ፈጥኖ ይሰማል የትኛውስ ይበልጣል?

*ተግባር*

- በምንጸልይበት ጊዜ እመቤታችንን መላእክቱንና ቅዱሳኑን እንዲያማልዱን እንጠይቃቸው።
- የጠባቂ መላእክቶቻችንን ምክር በመስማትና የቅዱሳንን በጎ ሥራዎች እንደ አርአያ በመውሰድ ዘወትር መከተል አለብን።
- በሰማያት ሆኖ ዘወትር የሚረዳንና የሚጠብቀን አንድ ወዳጅ ከቅዱሳን መሐል እናብጅ።

ይቆየን፡፡